# የወንጀል ቅጣት አወሳሰን በምስራቅ ሃረርጌ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

**ጋሻዬ መረሳ**

በዚህ ቅኝት በተዳሰሱት አራት የወንጀል አይነቶች ለመገንዘብ እንደተቻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው ከወጣ በኋላ ከወለል በታች የመቅጣት አዝማሚያ በስርቆት በቸልተኝነት ሰው መግደል እና በአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ከ7.75% እስከ 59.71% መጨመሩን ሲያሳይ በውምብድና ወንጀል ለውጥ አልታየም፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ከወለል በታች የተቀጡ ተከሳሾች መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ከ53 ጥፋተኞች 7(13.21%) ሲሆኑ ከመመሪያው በኋላ ከ54 ጥፋተኞች 20(37.03%) ናቸው፡፡ይህም ከመመሪያው መውጣት በኋላ በ25.17% መጨመሩን ያሳያል፡፡ (ሰንጠረዥ 2 እና 3ን ይመልከቱ)

ከቅጣት ደረጃ አንጻር ስንመለከት መመሪያው ከመውጣቱ በፊትም ሆነ በኋላ በአብዛኛው ቅጣቶች የሚወድቁት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ከመመሪያው በፊት በዝቅተኛ ደረጃ 37 (69.8%) በመካከለኛ ደረጃ 6 (11.32%)እና በከባድ ደረጃ 3 (5.66%)ተከሳሾች ተቀጥተዋል፡፡ከመመሪያው በኋላ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ 32 (59.25%) በመካከለኛ ደረጃ 2 (3.7%)ጥፋተኞች ተቀጥተዋል ፡፡ ከመመሪያው በኋላ ሁሉም ጥፋተኞች በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃዎች የተቀጡ ሲሆን በከባድ እና ከዛያ በላይ የተቀጣ የለም፡፡በአጠቃላይ በዝቅተኛ ቅጣት የማተኮር ሁኔታ ከመመሪያው በኋላ በ10.55% መቀነሱን ያሳያል፡፡ (ሰንጠረዥ 4 እና 5ን ይመልከቱ)

አማካይ የእስር ጊዜ በሁሉም ወንጀሎች የቀነሰ ሲሆን በአጠቃላይ ስናየው ከመመሪያው በፊት 5 አመት ከ6 ወር ከ16 ቀን ከ6 ሰዓት ሲሆን ከመመሪያው በኋላ 3 አመት ከ10 ወር ከ4 ቀን ከ6 ሰዓት ነው፡፡ ይህ ጊዜ ከመመሪያው በኋላ በ30.66% መቀነሱን ያሳያል፡፡